የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፴፪ኛ ዓመት ቁጥር ፰
አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፭ ቀን ፪ሺ፲፰

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32nd Year No. 8
ADDIS ABABA,24th December, 2025

**ማውጫ**

ደንብ ቁጥር ፭፻፹፪/፪ሺ፲፰
የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኤሌክትሮኒክ ፊርማ ደንብ……………......................................ገጽ ፲፱ሺ፬፻፲፮

**Content**

Regulation No. 582/2025
Council of Ministers Electronic Signature Regulations………………….................Page 19416

**ደንብ ቁጥር ፭፻፹፪/፪ሺ፲፰**

**የኤሌክትሮኒክስ ፊርማ ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በኤሌክትሮኒክ ፊርማ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፸፪/፪ሺ፲ (እንደተሻሻለ) አንቀፅ ፶፫ ንዑስ አንቀፅ (፩) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**REGULATION No. 582/2025**

**ELECTRONIC SIGNATURE REGULATION**

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Articles 53 Sub Article (1) of the Electronic Signature Proclamation No. 1072/2018 (as amended).

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ ድንጋጌዎች**

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኤሌክትሮኒክ ፊርማ ደንብ ቁጥር ፭፻፹፪/፪ሺ፲፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩/ "አመልካች" ማለት የሰርተፊኬት ሰጪነት፣ የሪፖዚቶሪ፣ የጊዜ ማህተም ወይም ሌሎች ተያያዥ አገልግሎቶች ለመስጠት ከሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣን ፈቃድ የሚጠይቅ አካል ነው፤

፪/ "የሰርተፊኬት ሰጪነት ፈቃድ" ማለት የሰርተፊኬት ሰጪነት፣ የሪፖዚቶሪ ፣የጊዜ ማህተም፣ የምስጠራ፣ የተገልጋይ ምዝገባ እና ማንነት ማጣራት አገልግሎትን በአንድነት መስጠት የሚያስችል በሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣን የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

**PART ONE**

**General Provisions**

1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Council of Ministers Electronic Signature Regulations No. 582/2025.

2. Definition

In this Regulation, unless the context otherwise requires:

1/ "Applicant" means a person who applies to the Root Certificate Authority to obtain a license to provide Certificate Service, Repository Service, Time Stamp Service, or other related services;

2/ "Certificate Provider License" means a license issued by the Root Certificate Authority for the provision of a certification service, repository, timestamp, encryption, user registration and identity verification services simultaneously;

፫/ "የምዝገባ እና ማንነት ማረጋገጥ አገልግሎት ፈቃድ" ማለት ሰርተፊኬት ጠያቂ ተገልጋዮች ለመመዝገብ በሚያቀርቡት ማስረጃ መሰረት ማንነታቸውን የማረጋገጥ እና የማጣራት አገልግሎት እንዲሰጥ በሰርተፊኬት ሰጪ አካል ውክልና የሚሰጠው አካል ነው፤

፬/ "የሪፖዚቶሪ አገልግሎት ፈቃድ" ማለት ሰርተፊኬቶችን ይፋ የማድረግ፣ የማከማቸት እና መልሶ የማግኘት አገልግሎት መስጠት የሚያስችል በሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣን የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

፭/ "አዋጅ" ማለት የኤሌክትሮኒክ ፊርማ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፸፪/፪ሺ፲ (እንደተሻሻለ) ነው፤

፮/ በአዋጁ አንቀፅ ፪ መሰረት ትርጉም የተሰጣቸው ቃላትና ሀረጎች ለዚህ ደንብም ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## ክፍል ሁለት

## ስለ ብሔራዊ የክሪፕቶ መሰረተ-ልማት ካውንስል

### ፫. ስለማቋቋም

፩/ ብሔራዊ የክሪፕቶ መሠረተ-ልማት ካውንስል (ከዚህ በኋላ "ካውንስል" ተብሎ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

፪/ ካውንስሉ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል።

### ፬. የካውንስሉ ዓላማ

የካውንስሉ ዋና ዋና ዓላማ በአዋጁና በዚህ ደንብ የተመለከቱትን ፈቃድ አሰጣጦች አስመልክቶ የሚነሱ አለመግባባቶችን በገለልተኝነት መርምሮ መወሰን እንዲሁም የክሪፕቶ ስርዓትን በመጠቀም ዘላቂና ደህንነቱ የተጠበቀ የዲጂታል አገልግሎት አቅርቦትን የሚያረጋግጡ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ማመላከት ነው።

3/ "Registration and Identity Verification Service License" means a body authorized by a certificate provider to provide identity authentication and verification services to certificate requesters based on the evidence they provide;

4/ "Repository Service License" means a license issued by the Root Certificate Authority enabling to disclose, store and retrieve certificates;

5/ "Proclamation" means the Electronic Signature Proclamation No. 1072/2018 (as amended);

6/ Definitions provided under Article 2 of the Proclamation shall be applicable to this Regulation.

## PART TWO

## National Crypto Infrastructure Council

### 3. Establishment

1/ The National Crypto Infrastructure Council (hereinafter referred to "The Council") is hereby established by this Regulation.

2/ The council shall be accountable to the Prime Minister.

### 4. Objective of the Council

The primary objective of the Council is to impartially examine and resolve disputes regarding licensing and accreditation processes as stipulated in the Proclamation and this Regulation, as well as to guide policy directions that ensure the sustainable and secure provision of digital certificate services utilizing cryptography.

## ፭. የካውንስሉ አባላት

፩/ ካውንስሉ ሰባት አባላት ይኖሩታል።

፪/ የምክር ቤቱ አባላት ከኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ጋር የጠበቀ ትስስር ያላቸው ሆነው፤ ሦስቱ ከመንግሥት ተቋማት፣ ሁለቱ ከግል ዘርፍ እንዲሁም ሁለቱ በዋናነት በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ላይ ትኩረት አድርገው ከሚያስተምሩ ዩኒቨርሲቲዎች የሚወከሉ ይሆናል።

፫/ አባላቱን ጨምሮ ከአባላቱ ውስጥ ሰብሳቢ እና ምክትል ሰብሳቢ በሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣኑ አቅራቢነት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾሙ ይሆናል።

## ፮. የካውንስሉ አባላት የሚመረጡበት መስፈርት

ማንኛውም ሰው የካውንስሉ አባል ሆኖ ለመመረጥ፡-

፩/ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው፤

፪/ በኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት ነዋሪ የሆነ፤

፫/ በሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣኑ የስልጣን ወሰን ውስጥ ከሚገኝ ማንኛውም ተቋም ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ የጥቅም ግጭት የሌለው፤ እና

፬/ በማጭበርበር፣ እምነት በማጉደል፣ በሙስና ወይም በኮምፒውተር ወንጀል ተከሶ ያልተቀጣ ወይም በነዚህ ወንጀሎች የተቀጣ ከሆነ ፍርዱን የጨረሰና የተሰየመ፡፡

## ፯. የካውንስሉ አባላት የሥራ ዘመን

፩/ የካውንስሉ አባላት የስራ ዘመን ሦስት ዓመት ይሆናል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም አንድ የካውንስል አባል ለአንድ ጊዜ በድጋሚ አባል ሆኖ ሊመረጥ ይችላል።

## 5. Members of the Council

1/ The Council shall have seven members.

2/ Members of this Council shall possess close affinity with Information Technology, comprising three representatives from governmental institutions, two representatives from the private sector, and two representatives from universities primarily focused on teaching in Information Technology.

3/ The members, including the Chairperson and Deputy Chairperson, shall be appointed by the Prime Minister upon the recommendation of the root certificate authority.

## 6. Requirement for selection of the members of The Council

To be appointed as a member of the Council, a person:

1/ Shall be Ethiopian Citizen;

2/ Shall be a permanent resident of Ethiopia;

3/ Has no direct or indirect conflict of interest in any Company subject to the Jurisdiction of the Root Certificate Authority;and

4/ Has not been convicted for fraudulent activities, breach of trust corruption or computer crime, or if convicted reinstated after completion of the punishment.

## 7. Terms of Members of the Council

1/ Members of the Council shall serve for a term of three years.

2/ Notwithstanding Sub-Article (1) of this article, a member of the Council may be re-appointed as a member for one additional term.

**፰. <u>የካውንስል አባል ከአባልነት ስለሚነሳበትና ስለሚለቅበት ሁኔታዎች</u>**

፩/ አንድ የካውንስል አባል በሚከተሉት ምክንያቶች ከአባልነት ሊነሳ ይችላል፡-

ሀ) በህመም ምክንያት ተግባሩን በአግባቡ መወጣት ካልቻለ፤

ለ) ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት በማጭበርበር፣ እምነት በማጉደል ወይም በሙስና ወንጀል ተከሶ የተፈረደበት ከሆነ፤

ሐ) የጥቅም ግጭት ከተከሰተ፤

መ) የብቃት ማነስ ካጋጠመው፤ወይም

ሠ) በራሱ ፈቃድ ከአባልነት ለመልቀቅ ሲያመለክት እና ማመልከቻው ተቀባይነት ሲያገኝ።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የካውንስል አባል የሶስት ወር የጽሁፍ ቅድመ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ከካውንስል አባልነት በፍላጎቱ ሊለቅ ይችላል።

፫/ ማንኛውም የካውንስል አባል በሞት ወይም ኃላፊነቱን በመልቀቁ ወይም ከኃላፊነቱ እንዲነሣ በመደረጉ ምክንያት የአባላት መጓደል በሚፈጠርበት ጊዜ በዚህ ደንብ መሰረት ተተኪው የካውንስል አባል ይሾማል።

**፱. <u>የካውንስሉ ስልጣንና ተግባር</u>**

ካውንስሉ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ ሰርተፊኬት ሰጪዎች፤ ሪፖዚቶሪዎች፣ የጊዜ ማህተም ወይም የምዝገባና ማንነት ማረጋገጥ አገልግሎት ሰጪዎች ከፍቃድ ወይም እውቅና አሰጣጥ፣ ዕድሳት፣ ስረዛና ከሌሎች አገልግሎቶች ጋር ተያይዞ ሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣኑ ላይ የሚያነሱትን ቅሬታዎች ይቀበላል፤ ቅሬታውን መርምሮ ተገቢ ውሳኔ ይሰጣል።

**8. <u>Conditions for Removal or Resignation of Members of the Council</u>**

1/ A Council member may be removed from membership for the following reasons:

a) Inability to perform his duties due to health issues;

b) If he has been criminally convicted of fraudulent activities, breach of trust or corruption by a court of competent jurisdiction;

c) If conflict of interest occurs;

d) Due to incompetence and;

e) Upon the acceptance of voluntary resignation written request.

2/ Without prejudice to Sub-Article 1 of this Article, any member of the council can resign from the Council after providing a three month notice in advance.

3/ In the event of a vacancy in the membership of the Council due to the death, voluntary resignation, or removal from office of any member, a successor Council member shall be appointed in accordance with the provisions of this Regulation.

**9. <u>Power and Duties of the Council</u>**

The Council shall have the following Power and duties to:

1/ Receives and settle complaints of Certificate, Repository, Time Stamp Service, and Registration and Identity Verification Service Providers on the decision of Root Certificate Authority regarding License issuance, renewal, suspension, and other related services.

፪/ ከሰርተፊኬት ፍቃድ ወይም እውቅና አሰጣጥ፣ ዕድሳት፣ ስረዛና አጠቃላይ ከክሪፕቶ መሰረተ ልማት አገልግሎቶች ጋር ተያያዥ የሆኑ ክፍተቶች ላይ በመምከር የፖሊሲ አቅጣጫ ያስቀምጣል።

## ፲. የካውንስሉ የስብሰባ እና የአሰራር ሥነ-ሥርዓት

፩/ ካውንስሉ በዓመት ሁለት ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም በሰብሳቢው ጥሪ ወይም ሁለት ሦስተኛው የምክር ቤቱ አባላት ሲጠይቁ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፡፡

፪/ በስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ የካውንስሉ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

፫/ የካውንስሉ ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ሰብሳቢው ሰብሳቢውን ወክሎ ይሰራል፡፡

፬/ የካውንስሉ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ።ድምፁ እኩል ለእኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።

፭/ ካውንስሉ በሚያደርጋቸው ስብሰባዎች ሙያዊ ድጋፋቸው ያስፈልገኛል ብሎ ካመነባቸው በውሳኔዎች ላይ ድምፅ መስጠት የማይችሉ ሙያተኞችን በሰብሳቢው በኩል መጋበዝ ይችላሉ።

፮/ ካውንስሉ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፲፩. የካውንስሉ አባላት የማትጊያ ክፍያና አቅርቦት

ሩት ሰርተፊኬት ባለሥልጣኑ፡-

፩/ የካውንስሉ ሴክሬታሪያት በመሆን ለስራ የሚያስፈልገውን አቅርቦት ያቀርባል።

፪/ የካውንስሉ አባላት የማትጊያ ክፍያ በገንዘብ ሚኒስቴር በሚጸደቅ መመሪያ ክፍያ ይፈፅማል።

2/ Set policy directions regarding gaps in certificate licensing or accreditation, renewal, revocation, and overall cryptographic infrastructure services.

## 10. Meeting and Working Procedure of the Council

1/ The Council shall convene twice annually; however, it may convene at any time upon the call of the Chairperson or at the request of two-thirds of the Council members.

2/ The presence of more than half of the Council members shall constitute a quorum for a meeting.

3/ In the absence of the Chairperson of the Council, the Vice-Chairperson shall act on behalf of the Chairperson.

4/ Decisions of the Council shall be passed by a majority vote. In the event of a tie, the Chairperson shall have a casting vote.

5/ The Council may, through the Chairperson, invite professionals it believes are necessary for their professional support to its meetings; however, such professionals shall not have the right to vote on decisions.

6/ The Council may issue its own rules of procedure for its meetings.

## 11. Remuneration and Resources for Council Members

The root certificate authority:

1/ Acts as the Secretariat of the Council and provide the necessary logistic for its functions.

2/ Provide the necessary remuneration to the Council Members to fulfill their duties, as approved by the Ministry of Finance.

## ክፍል ሶስት

## የቅሬታ አፈታት ሥነ-ሥርዓት

### ፲፪. ቅሬታ የሚቀርብበት ግዜ

ሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣን በሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርብ ቅሬታ ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በሠላሳ (፴) ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ለካውንስሉ መቅረብ አለበት።

### ፲፫. ቅሬታ የሚስተናገድበት ስነ-ስርዓት

፩/ ለካውንስሉ የሚቀርብ ቅሬታ በፅሁፍ ሆኖ አስፈላጊ መረጃዎችን መግለጽ አለበት።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚቀርብ ቅሬታ፡-

ሀ) የሩት ሰርተፍኬት ባለስልጣኑ እና የቅሬታ አቅራቢ ሙሉ ስምና አድራሻ፤

ለ) የክርክሩ ባህሪ መግለጫ፤

ሐ) የሚጠየቀው ውሳኔ፤ እና

መ) ሌላ አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች፤ መያዝ አለበት።

፫/ ካውንስሉ ቅሬታውን በተቀበለ በአምስት (፭) ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ለሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣኑ የቅሬታውን ግልባጭ መላክ አለበት።

፬/ ሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣኑ የቅሬታው ቅጂ በደረሰው በአስራ አምስት (፲፭) ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ምላሽ መስጠት አለበት። ምላሹን ካልሰጠ ካውንስሉ የቀረበለትን ቅሬታ መሰረት በማድረግ ይወስናል።

፭/ ካውንስሉ ቅሬታው በቀረበ በስልሳ (፷) ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት።

፮/ ካውንስሉ የሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣኑን ውሳኔ ያጸናበት፣ የሻረበትን ወይም እንደገና እንዲታይ ያዘዘበትን ምክንያት በማብራራት ውሳኔውን በጽሁፍ ለቅሬታ አቅራቢ ማሳወቅ አለበት።

## PART THREE

## Dispute Settlement Procedure

### 12. Complaint Period

A complaint to be lodged against the decision of the Root Certificate Authority shall be submitted to the council within thirty (30) consecutive working days from the date the decision is given.

### 13. Complaint Handling Procedure

1/ Any complaint lodged to the Council shall be in writing, and contain relevant information.

2/ A complaint that is lodged as per Sub-Article (1) of this Article shall contain:

a) The full address of the Compliant and Root Certificate Authority;

b) A statement of the nature of the dispute;

c) The relief sought; and

d) any other relevant evidences.

3/ The Council shall, within five (5) consecutive working days of the receipt of the complaint, send a copy of the complaint to Root Certificate Authority.

4/ The Root Certificate Authority shall give its response within (15) fifteen consecutive working days after receiving the complaint. Failure to do so shall result in the Council making a decision based on the complaint as submitted.

5/ The Council, shall deliver its decision within sixty (60) consecutive working days from the date of the complaint.

6/ The Council shall notify the complainant in writing of its decision, elaborating on the reasons for upholding, reversing, or ordering the reconsideration of the Root Certificate Authority's decision.

፯/ ካውንስሉ የቀረበለትን ቅሬታ በፌደራል አስተዳደር ሥነ-ስርዓት አዋጅ እና በፍትሐ ብሔር ሥነ ስርዓት ህጎች መሰረት አድርጎ ይመራል።

**፲፬. <u>የጥቅም ግጭት</u>**

፩/ ማንኛውም የካውንስሉ አባል በመታየት ላይ ከሚገኝ ቅሬታ ጋር የጥቅም ግጭት ያለበት እንደሆነ ጉዳዩን ማየት አይችልም።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የጥቅም ግጭት መኖር እና አለመኖሩን ቀሪ የካውንስል አባላት በድምጽ ብልጫ ይወስናሉ።

**፲፭. <u>ስለ ይግባኝ</u>**

፩/ በካውንስሉ ውሳኔ ቅር የተሰኘ አካል ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በስልሳ (፷) ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል።

፪/ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ ላይ ፍሬ ነገርን አስመልክቶ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።

**<u>ክፍል አራት</u>**

**<u>ስለ ሰርተፊኬት ሰጪዎች ፋይናንስ፣ የስርዓትና ምርት ደህንነት ደረጃ</u>**

**፲፮. <u>ስለ ፋይናንስ አቅም</u>**

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፳፯ መሰረት አንድ የሰርተፊኬት ሰጪነት ፈቃድ ለማግኘት የሚያመለክት ሰው አስተማማኝ የፋይናንስ አቅም አለው የሚባለው፡-

ሀ) በሀገር ውስጥ ባንክ የተቀመጠና ከዕዳ ነጻ የሆነ ገንዘብ ብር ፪፻፴፪ ሚሊዮን ብር (ሁለት መቶ ሰላሳ ሁለት ሚሊዮን ብር) የባንክ ሂሳብ ቅጂ፣ወይም

7/ The Council shall conduct its proceedings regarding any complaint submitted to it in accordance with the Federal Administrative Procedure Proclamation and the Civil Procedure Laws.

**14. <u>Conflict of Interest</u>**

1/ A council member that has a conflict of interest with a complaint shall not entertain the cases.

2/ The remaining Council members shall decide by vote whether there is a conflict of interest or not in accordance with Sub-Article (1).

**15. <u>Request of Appeal</u>**

1/ A party who is aggrieved by the decision of the Council may appeal to the Federal High Court within sixty (60) consecutive working days from the date the decision is given.

2/ The ruling given by the Federal High Court on the substantive merits of an appeal shall be final.

**<u>PART FOUR</u>**

**<u>Certificate Providers Financial, System and Product Requirements</u>**

**16. <u>Financial Requirements</u>**

1/ According to Article 27 of the Proclamation, a person who applies for a Certificate Provider license shall be deemed to have reliable financial capacity if he is able to provide:

a) A copy of bank statement with deposit Birr 232,000,000 (Two Hundred Thirty –Two Million Birr) in a local bank account which is free from any debt or claim; or

ለ) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ፊደል ተራ (ሀ) ላይ ከተመላከተው ገንዘብ ጋር ተመጣጣኝ መሆኑ በባለሙያ በጥናት የተረጋገጠ እና ከስራው ጋር ቀጥተኛ ዝምድና ያለው በአይነት የሚቀርብ ማስያዣ፤ እና

ሐ) ከሰርተፊኬት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ለሚያደርሰው ጉዳት ሽፋን የሚሆን እስከ ብር ፳ ሚሊዮን ብር (ሃያ ሚሊዮን ብር) የሚደርስ የመድን ዋስትና ቅጂ፤ ማስረጃ ማቅረብ የቻለ እንደሆነ ነው።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ለ) መሰረት አመልካች በአይነት ብቻ ካፒታል የሚያቀርብ ከሆነ በአይነት የሚቀርበው ሀብት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሀ) ከተጠቀሰው የገንዘብ መጠን ማነስ የለበትም።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) መሰረት በገንዘብ ወይም በዓይነት የሚቀርብ የፋይናንስ አቅም በማሳገድ ማረጋገጫ ለሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣኑ መቅረብ አለበት።

፬/ ሰርተፊኬት ሰጪው ለተገልጋዮች ከሚሰጣቸው ሰርተፊኬቶች ከሚሰበስበው ጠቅላላ ገቢ ፪ በመቶውን የክሪፕቶ ስርዓቱን ተዓማኒነት እና አጠቃላይ ደህንነት ለማረጋገጥ ለሚከናወኑ ተግባራት እንዲውል ለሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣን ገቢ ያደርጋል።

## ፲፯. <u>የመድን ዋስትና ጥቅም ላይ ስለሚውልበት ሁኔታ</u>

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፮ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሐ) ላይ የተመለከተው የመድን ዋስትና ጥቅም ላይ የሚውለው፡-

ሀ) በሰርተፊኬት ሰጪ ጥፋት ተገልጋይ ወይም እምነት የሚያሳድሩ አካላት ላይ ለሚያደርስ ጉዳት ካሳ ክፍያ፤ ወይም

b) A security deposit provided in kind, the equivalence of which to the money specified in Sub-Article (1) (a) of this article is verified by professional study and which has a direct relationship with the work;

c) An insurance Policy with Birr 20,000,000 (Twenty Million Birr) to cover any damage resulted in the process of providing a Certification Service.

2/ If the applicant brings the capital only in kind as per Sub-Article (1) (b) of this Article, the capital should not be less than the finance resource stated in Sub-Article (1) (a) of this Article.

3/ The financial capacity, whether provided in cash or in kind, based on Sub-Article (1) letters (a) and (b) of this article, shall be blocked and confirmation shall be submitted to the Root Certificate Authority.

4/ The Certificate Provider shall pay 2 percent of the gross revenue it collects from the certificate it issues to the Root Certificate Authority to be used for activities that ensure the integrity and overall security of the crypto system.

## 17. <u>Conditions for Insurance Policy Usage</u>

1/ The insurance Policy which is indicated under Article 16 Sub-Article (1) (c) of this Regulation shall be used:

a) as a compensation when Certificate Provider causes damage to a subscriber or a relying party; and

ለ) ሰርተፊኬት ሰጪው ስራውን በሚያቋርጥበት ወቅት ተገልጋዮችን ወደ ሌሎች ሰርተፊኬት ሰጪዎች ለማዘዋወር እንደሆነ ነው።

፪/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሐ) ላይ የተመለከተው የመድን ዋስትና በየዓመቱ መታደስ ይኖርበታል።

፲፰. <u>የሰርተፊኬት ሰጪዎች ፋይናንስ አቅም ስለማሻሻል</u>

ሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣኑ ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዚህ ክፍል የተገለፁ የፋይናንስ እና ዋስትና ገንዘብ መጠንን አስመልክቶ በመመሪያ ማሻሻል ይችላል።

፲፱. <u>የሰርተፊኬት ሰጪዎች ሥርዓትና የምርቶች ደህንነትና አስተማማኝነት መመዘኛዎች</u>

፩/ ሰርተፊኬት ሰጪ አገልግሎት ሲያቀርብ የሚጠቀመውን ስርዓትና ምርት ደህንነትና አስተማማኝነት ለመመዘን ሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣኑ የሰርተፊኬት ሰጪን፡-

ሀ) የገንዘብ አቅምና የሰው ኃብት አቅም፣

ለ) የሃርድዌርና ሶፍትዌር አስተማማኝነት እና ስርዓት ደረጃ፣

ሐ) አገልግሎቱ የሚያከናውንበት የዳታ ማዕከል አካላዊ ደህንነት፣

መ) አገልግሎትን ለመስጠት ተግባራዊ የሚሆነው የስነ-ስርዓት ደህንነት፣

ሠ) በሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣኑ ወይም በሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣኑ እውቅና ያለው ወይም የተሰጠው ኦዲተር ይፋ የሚያደርገው የደህንነት ኦዲት ግኝት፣ እና

ረ) የስርዓቱ ዓለም አቀፍ ተጣጣሚነት በሚመለከት መመሪያ ያወጣል።

b) to transfer Subscribers to other Certificate Provider when Certificate Provider discontinue his service.

2/ The insurance Policy which is indicated under Article 16 Sub-Article (1) (c) of this Regulation shall be subjected to renewal every year.

18. <u>**Modification of Financial Requirements of Certificate Service Provider**</u>

Root Certificate Authority, taking in to account the changing circumstances, may amend the Financial and Insurance requirement of Certificate Provider in a Directive.

19. <u>**Qualification of the Security and Trustworthiness of a Certificate Provider**</u>

1/ The security and trustworthiness of the system and product, which any Certificate Service Provider use to render services, shall be evaluated based on the standards the Root Certificate Authority issues on the following areas:

a) Capital and human resource capabilities;

b) The security level of hardware and software systems;

c) The physical security of its data center;

d) The security level of the system used to render the service;

e) Audit findings issued by the Root Certificate Authority or by an auditor recognized by Root Certificate Authority; and

f) The interoperability of its system to an international standard.

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣኑ በመመሪያ ሌሎች አግባብነት ያላቸው መስፈርቶች ሊያወጣ ይችላል።

**፳. ለውጪ ሀገር ሰርተፊኬት ሰጪዎች ስለሚሰጥ እውቅና**

ሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣን ለውጪ ሃገር ሰርተፊኬት ሰጪዎች እውቅና ሲሰጥ በቅድሚያ፡-

፩/ በተቋቋመበት ሀገር አግባብ ካለው አካል የሰርተፊኬት ሰጪነት ፈቃድ ወይም እውቅና የተሰጠው መሆኑን አግባብነት ካለው የኢትዮጵያ የመንግስት አካል ማረጋገጫ ማቅረቡን፤

፪/ በኢትዮድያ ውስጥ ሰርተፊኬት ሰጪነት አገልግሎት የሚያከናውን ወኪል ያቋቋመ መሆኑን፤ እና

፫/ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸው ስታንዳርዶችን ጨምሮ አዋጁን እና አዋጁን ተከትለው የወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን አክብሮ ለመስራት አስገዳጅ የውል ስምምነት ለመግባት ፈቃደኛ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል።

**ክፍል አምስት**

**ስለሪፖዚቶሪ፣ የጊዜ ማህተም እና የምዝገባና ማንነት ማጣራት አገልግሎት ሰጪዎች ፍቃድ አሰጣጥ**

**፳፩. ስለሪፖዚቶሪ አገልግሎት ሰጪዎች ፍቃድ**

፩/ ማንኛውም ሰርተፊኬት ሰጪ በራሱ ወይም በአዋጁና በዚህ ደንብ መሰረት በተዘረጉ ስርዓቶች ፈቃድ በተሰጠው ሰው አማካኝነት የሪፖዚቶሪ አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት።

2/ Without prejudice to Sub-Article 1 of this Article, the Root Certificate Authority may issue a Directive to set other relevant requirements.

**20. Recognition of Foreign Certificate Provider**

When granting recognition to Foreign Certificate Providers, the Root Certificate Authority must first confirm that:

1/ Providing confirmation from the relevant Ethiopian government body that it has been granted a certificate issuance license or recognition by the appropriate authority in its country of establishment;

2/ Establish an agency in Ethiopia to provide Certification Service; and

3/ Agree to enter into a binding contractual agreement to comply with the Proclamation, Regulations and Directives issued pursuant to the Proclamation, including internationally accepted standards.

**PART FIVE**

**Repository, Time Stamp and Registration and Identity Verification Service Provider License Issuance**

**21. Repository Service Providers License**

1/ Any Certificate Service Provider shall be obliged to provide Repository Service either by itself or through a person licensed under the systems established in accordance with the Proclamation and this Regulation.

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደተጠበቀ ሆኖ በሪፖዚቶሪ አገልግሎት ላይ ብቻ መሰማራት የሚፈልግ አመልካች ማመልከቻውን ለሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣኑ በማቅረብ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል።

**፳፪. <u>የሪፖዚቶሪ አገልግሎት ሰጪ ፍቃድ ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>**

ሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣኑ፡-

፩/ የሪፖዚቶሪ አገልግሎት ፍቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻን በተመለከተ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፤

፪/ ፍቃድ ያገኙ የሪፖዚቶሪ አገልግሎት ሰጪዎችን ዝርዝር በድረ- ገፁ ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል።

**፳፫. <u>የሪፖዚቶሪ አገልግሎት ፍቃድ አሰጣጥ</u>**

፩/ ሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣን የሚቀርብለትን የሪፖዚቶሪ አገልግሎት ፍቃድ ማመልከቻ የሚከተሉትን መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ እና በመመርመር፡-

ሀ) ለሚደርስ ጉዳት የሚውል የመድን ዋስትናን ጨምሮ የፋይናንስና ካፒታል አቅም፤

ለ) የሰው ሃይል ቁጥር እና የትምህርት ደረጃ፤

ሐ) የሃርድዌርና ሶፍትዌር ስርዓት ደረጃ፤

መ) አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልገው እውቀትና ተያያዥ ልምድ፤

ሠ) አገልግሎቱን ለመስጠት የሚከተለው ስነ-ስርዓት ደህንነት፤

ረ) የመስሪያ ቦታ ደህንነት፤

ሰ) የግል መረጃ ጥበቃና አጠቃላይ የመረጃ አያያዝ ደህንነት ፖሊሲዎች፤

ሸ) የአደጋ ማገገሚያ እና የስራ ቀጣይነት ስትራቴጂ ፍቃድ ይሰጣል።

2/ Without prejudice Sub-Article (1) of this Article, any person who wants to engage only as Repository Service Provider may lodge application to the Root Certificate Authority.

**22. <u>Application for RepositoryService Providers License</u>**

The Root Certificate Authority shall:

1/ Issues detail directive regarding Repository Service Provider license application;

2/ List of licensed time-stamping service providers on its website.

**23. <u>Repository Service Provider Licensing</u>**

1/ The Root Certificate Authority shall examine and provide license for Repository Service License Application submitted based on the following requirements:

a) The required finance and capital capacity including insurance bond for future damage;

b) The required manpower and educational level;

c) The required hardware and software system;

d) The required knowledge and related experience to provide service;

e) The required system security to provide service;

f) The security of the service center;

g) Policies pertaining to custody of information security and personal data protection;

h) disaster recovery and work continuity strategy.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተመለከቱ መስፈርቶችን በተመለከተ ሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣን ዝርዝር መመሪያ ያወጣል።

**፳፬. <u>የሪፖዚቶሪ ፍቃድ የማያሰጡ ሁኔታዎች</u>**

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተደነገገው ቢኖርም፤ የሪፖዚቶሪ ፍቃድ እንዲሰጠው ማመልከቻ ያቀረበው አካል፡-

ሀ) የተፈጥሮ ሰው፤

ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ ያልተቋቋመ ተቋም፤ ወይም

ሐ) በወንጀል የተፈረደበት ሆኖ የወንጀል ቅጣቱን ከፈጸመ በኋላ ያልተሰየመ፤ እንደሆነ ዝርዝር ምርመራ ሳያስፈልግ ማመልከቻው ውድቅ ይሆናል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ፍቃድ የማያሰጡ ሌሎች ሁኔታዎችን በተመለከተ ሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣን መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

**፳፭. <u>የሪፖዚቶሪ ፍቃድ ዘመንና ተያያዥ ጉዳዮች</u>**

፩/ የሪፖዚቶሪ ፍቃድ ወይም እውቅና ያገኘ አገልግሎት ሰጪ ፍቃዱ ለአምስት (፭) አመታት የሚያገለግል ይሆናል።

፪/ የሪፖዚቶሪ ፍቃድ ስለሚታደስበት፣ ስለሚታገድበት፣ ስለሚሰረዝበት፣ ስለሚመለስበት እንዲሁም የፍቃድ መሰረዝ ውጤትን አስመልክቶ እንደአግባብነቱ በአዋጁ አንቀፅ ፲፫ ጀምሮ እስከ ፲፯ ያሉ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

2/ The Root Certificate Authority shall issue detail Directive regarding requirements identified on Sub-Article (1) of this Article.

**24. <u>Conditions for Denying License</u>**

1/ Notwithstanding Article 23 Sub-Article (1) of these Regulations, any application to Repository License shall be rejected, without going into detail screening, if the applicant:

a) Is a natural person;

b) Is a body corporate not established in Ethiopia; or

c) Has been convicted of an offence and not reinstated after the completion of the punishment.

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, the Root Certificate Authority may prescribe Directive for additional qualification requirements to deny a license.

**25. <u>License Period and Related Matters</u>**

1/ A Licensed or recognized Repository Services Provider license is valid for five years.

2/ The provisions of Article 13 through 17 of the Proclmation regarding license renewal, suspension,cancellation, and return, as well as the consequences of cancellation, shall as appropriate, apply to a repository license.

## ፳፮. የሪፖዚቶሪ አገልግሎት ሰጪ ግዴታዎች

፩/ ማንኛውም የሪፖዚቶሪ አገልግሎት ሰጪ፡-

ሀ) አገልግሎቱን በሚሰጥበት ጊዜ ደህንነቱ የተጠበቀና አስተማማኝ ሥርዓትና ምርቶችን የመጠቀም ሃላፊነት፤

ለ) በሶፍትዌር፣ ሃርድዌር ወይም ስልተ ቀመር ላይ ማንኛውም ለውጥ ወይም ማሻሻያ ከማድረጉ በፊት ሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣኑን ማስፈቀድ፤

ሐ) አስፈላጊ መረጃ ለተገልጋዮች ወይም እምነት ለሚያሳድሩ አካላት በቀላሉ ተደራሽ ማድረግ በሚቻል መልኩ የመያዝ፤

መ) ሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣኑ ወይም ሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣኑ ፍቃድ የሚሰጠው ኦዲተር ኦዲት ሲያደርግ የመተባበር፤

ሠ) ለተገልጋዮችና እምነት ለሚያሳድሩ አካላት ይፋ መሆን ያለባቸውን መረጃዎች ጊዜውን ጠብቆ ይፋ የማድረግ፤

ረ) ከሚሰጠው አገልግሎት ጋር የሚገናኙ መረጃዎችን ለሁለት ዓመት ጠብቆ የማቆየት ግዴታ አለበት።

፪/ ማንኛውም የሪፖዚቶሪ አገልግሎት ሰጪነት ፍቃድ ለማግኘት ማመልከቻ የሚያቀርብ አመልካች ትክክለኛና የተሟላ መረጃ የመስጠት ሀላፊነት አለበት።

## 26. Obligations of Repository Service Provider

1/ Any repository service provider has obligations:

a) To use a secured and trustworthy system and product while providing the service;

b) To request permission from the Root Certificate Authority before making any modification to the hardware, software system or algorithm;

c) To retain information in a way that is easily accessible to the Subscriber and Relying Party;

d) To cooperate for audit to be conducted by the Root Certificate Authority or an Auditor authorized by the Root Certificate Authority;

e) To publish all relevant information to Subscriber and Relying Party on time;

f) Retain information related to the provided service for two years.

2/ Any applicant lodging an application to engage as a Repository Service Provider shall submit accurate and adequate information.

**፳፯. የሪፖዚቶሪአገልግሎት ሰጪዎች ተጠያቂነት ና ቅጣት**

፩/ በሕግ ወይም በውል ስምምነት የተቀመጡ ሌሎች ሃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ሪፖዚቶሪ አገልግሎት ሰጪ በአዋጁ እና በዚህ ደንብ እንዲሁም ደንቡን ተከትለው በሚወጡ መመሪያዎች ላይ የተቀመጡ ግዴታዎችን ባለመወጣቱ ምክንያት ለሚያደርሰው ጉዳት ተጠያቂ ይሆናል።

፪/ ማንኛውም የሪፖዚቶሪ አገልግሎት ሰጪ የፀና ፍቃድ ሳይኖረው፤ ወይም በታገደ ፈቃድ የሪፖዚቶሪ አገልግሎቶችን የሰጠ እንደሆነ ወይም ከሚሰጠው አገልግሎት ጋር ተያይዞ መረጃዎችን ለሁለት ዓመት ይዞ ካልቆየ ከ ብር አንድ መቶ ሺህ እስከ ሁለት መቶ ሺህ ይቀጣል።

**፳፰. ስለጊዜ ማህተም አገልግሎት ሰጪነት ፍቃድ**

፩/ ማንኛውም ሰርተፊኬት ሰጪ በራሱ ወይም በአዋጁና በዚህ ደንብ መሰረት በተዘረጉ ስርዓቶች ፈቃድ በተሰጠው ሰው አማካኝነት የጊዜ ማህተም አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደተጠበቀ ሆኖ የጊዜ ማህተም አገልግሎት ላይ ብቻ መሰማራት የሚፈልግ አመልካች ማመልከቻውን ለሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣኑ በማቅረብ ፍቃድ ማግኘት ይኖርበታል።

**፳፱. የጊዜ ማህተም አገልግሎት ሰጪፍቃድ ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ**

ሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣኑ፡-

፩/ የጊዜ ማህተም አገልግሎት ፍቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻን በተመለከተ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፤

፪/ ፍቃድ ያገኙ የጊዜ ማህተም አገልግሎት ሰጪዎችን ዝርዝር በድረ - ገፁ ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል።

**27. Liability and Penalty of Repository Service Providers**

1/ Without prejudice to other liabilities provided by contract or law, any repository service provider who fails to meet its obligation under the Proclamation, these Regulations, and Directive issued following the Regulation shall be liable for the damage.

2/ Any repository service provider shall be penalized with a fine ranging from one hundred thousand Birr to two hundred thousand Birr if they operate repository services without a valid license; or if they operate repository services with a suspended license; or if they fail to retain information related to the provided service for two years.

**28. Time Stamp Service License**

1/ Any certificate authority is obligated to provide time stamp services, either directly or through a person authorized by it, in accordance with procedures stated in the proclamation and this regulation.

2/ Without prejudice Sub Article (1) of these Regulations, any person who wants to engage only as Timestamp Service Provider may lodge its application to the Root Certificate Authority.

**29. Application for Time Stamp Providers License**

The Root Certificate Authority shall:

1/ Issues detail directive regarding time stamp Service Provider license application;

2/ list licensed time-stamping service providers on its website.

**፴. <u>የጊዜ ማህተም አገልግሎት ፍቃድ አሰጣጥ</u>**

፩/ ሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣን የሚቀርብለትን የጊዜ ማህተም አገልግሎት ፍቃድ ማመልከቻ የሚከተሉትን መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ እና በመመርመር፡-

ሀ) ለሚደርስ ጉዳት የሚውል የመድን ዋስትናን ጨምሮ የፋይናንስና ካፒታል አቅም፤

ለ) የሰው ሃይል ቁጥር እና የትምህርት ደረጃ፤

ሐ) የሃርድዌርና ሶፍትዌር ስርዓት ደረጃ፤

መ) አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልገው እውቀትና ተያያዥ ልምድ፤

ሠ) አገልግሎቱን ለመስጠት የሚከተለው ስነ-ስርዓት ደህንነት፤

ረ) የመስሪያ ቦታ ደህንነት፤

ሰ) የግል መረጃ ጥበቃና አጠቃላይ የመረጃ አያያዝ ደህንነት ፖሊሲዎች፤እና

ሸ) የአደጋ ማገገሚያ እና የስራ ቀጣይነት ስትራቴጂ ፈቃድ ይሰጣል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተመለከቱ መስፈርቶችን በተመለከተ ሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣን ዝርዝር መመሪያ ያወጣል።

**፴፩. <u>የጊዜ ማህተም ፍቃድ የማያሰጡ ሁኔታዎች</u>**

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተደነገገው ቢኖርም፤ የጊዜ ማህተም ፍቃድ እንዲሰጠው ማመልከቻ ያቀረበው አካል፡-

ሀ) የተፈጥሮ ሰው፤

ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ ያልተቋቋመ ተቋም፤ ወይም

**30. <u>Time Stamp Provider Licensing</u>**

1/ The Root Certificate Authority shall examine and provide license for Time Stamp Service License Application submitted based on the following requirements:

a) the required finance and capital capacity including insurance bond for future damage;

b) the required manpower and educational level;

c) the required hardware and software system;

d) the required knowledge and related experience to provide service;

e) the required system security to provide service;

f) the security of the service center;

g) policies pertaining to custody of information security and personal data protection; and

h) disaster recovery and work continuity strategy.

2/ The Root Certificate Authority shall issue a detail Directive regarding requirements identified on Sub-Article (1) of this Article.

**31. <u>Conditions for Denying License</u>**

1/ Notwithstanding Article 30 Sub-Article (1) of these Regulations, any application to Time Stamp License shall be rejected, without going into detail screening, if the applicant:

a) Is a natural person;

b) Is a body corporate not established in Ethiopia; or

ሐ) በወንጀል የተፈረደበት ሆኖ የወንጀል ቅጣቱን ከፈጸመ በኋላ ያልተሰየመ፤ እንደሆነ ዝርዝር ምርመራ ሳያስፈልግ ማመልከቻው ውድቅ ይሆናል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ፍቃድ የማያሰጡ ሌሎች ሁኔታዎችን በተመለከተ ሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣን መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

## ፴፪. <u>የጊዜ ማህተም ፍቃድ ዘመንና ተያያዥ ጉዳዮች</u>

፩/ የጊዜ ማህተም ፈቃድ ወይም እውቅና ያገኘ አገልግሎት ሰጪ ፍቃዱ ለአምስት (፭) አመታት የሚያገለግል ይሆናል።

፪/ የጊዜ ማህተም ፈቃድ ስለሚታደስበት፣ ስለሚታገድበት፣ ስለሚሰረዝበት፣ ስለሚመለስበት እንዲሁም የፍቃድ መሰረዝ ውጤትን አስመልክቶ እንደአግባብነቱ በአዋጁ አንቀፅ ፲፫ ጀምሮ እስከ ፲፯ ያሉ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

## ፴፫. <u>የጊዜ ማህተም አገልግሎት ሰጭ ግዴታዎች</u>

፩/ ማንኛውም የግዜ ማህተም አገልግሎት ሰጪ፡-

ሀ) አገልግሎቱን በሚሰጥበት ጊዜ ደህንነቱ የተጠበቀና አስተማማኝ ሥርዓትና ምርቶችን የመጠቀም ሃላፊነት፤

ለ) በሶፍትዌር፣ ሃርድዌር ወይም ስልተ ቀመር ላይ ማንኛውም ለውጥ ወይም ማሻሻያ ከማድረጉ በፊት ሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣኑን ማስፈቀድ፤

ሐ) ሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣኑ ወይም ሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣኑ ፈቃድ የሚሰጠው ኦዲተር ኦዲት ሲያደርግ የመተባበር፤ ግዴታ አለበት።

c) Has been convicted of an offence and not reinstated after the completion of the punishment.

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, the Root Certificate Authority may prescribe a Directive for additional qualification requirements to deny a license.

## 32. <u>License Period Related Matters</u>

1/ A Licensed or recognized Time Stamp Services Provider license is valid for five years.

2/ The provisions of Articles 13 through 17 of the Proclamation regarding license renewal, suspension, cancellation, and return, as well as the consequences of cancellation, shall, as appropriate, apply to a Time Stamp license.

## 33. <u>Obligations of Time Stamp Service Provider</u>

1/ Any Time Stamp Service Provider has the obligations:

a) To use a secured and trustworthy system while providing the service;

b) To request permission from the Root Certificate Authority before making any modification to the hardware, software and algorithm of the system;

c) To cooperate while Root Certificates Service Provider or a licensed Auditor conduct auditing.

፪/ ማንኛውም የጊዜ ማህተም አገልግሎት ሰጪነት ፈቃድ ለማግኘት ማመልከቻ የሚያቀርብ አመልካች ትክክለኛና የተሟላ መረጃ የመስጠት ሀላፊነት አለበት።

## ፴፬. <u>የጊዜ ማህተም አገልግሎት ሰጪዎች ተጠያቂነትና ቅጣት</u>

፩/ የጊዜ ማህተም አገልግሎት ሰጪ በአዋጁ እና በዚህ ደንብ እንዲሁም ደንቡን ተከትለው በሚወጡ መመሪያዎች ላይ የተቀመጡ ግዴታዎችን ባለመወጣቱ ምክንያት ለሚያደርሰው ጉዳት ሃላፊ ይሆናል።

፪/ ማንኛውም የጊዜ ማህተም አገልግሎት ሰጪ የፀና ፈቀድ ሳይኖረው፣ ወይም በታገደ ፈቃድ የጊዜ ማህተም አገልግሎቶችን የሰጠ እንደሆነ ወይም ከሚሰጠው አገልግሎት ጋር ተያይዞ መረጃዎችን ለሁለት ዓመት ይዞ ካልቆየ ከብር አንድ መቶ ሺህ እስከ ሁለት መቶ ሺህ ይቀጣል።

## ፴፭. <u>ስለ ምዝገባና ማንነት ማጣራት አገልግሎት ሰጪነት ፍቃድ</u>

፩/ ማንኛውም ሰርተፊኬት ሰጪ በራሱ ወይም በውክልና የምዝገባ እና ማንነት ማጣራት አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደተጠበቀ ሆኖ የምዝገባ እና ማንነት ማጣራት ላይ ብቻ መሰማራት የሚፈልግ አመልካች ማመልከቻውን ለሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣኑ በማቅረብ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል።

2/ Any applicant applying for a time stamp service provider license shall have the duty to provide accurate and complete information.

## 34. <u>Liability and Penalty of Time Stamp ServiceProviders</u>

1/ Without prejudice to other liabilities provided by contract or law, any time stamp service provider who fails to meet its obligation under the Proclamation, these Regulations, and Directive issued following the Regulation shall be liable for the damage.

2/ Any time stamp service provider shall be penalized with a fine ranging from one hundred thousand Birr to two hundred thousand Birr if they operate time stamp services without a valid license; or if they operate time stamp services with a suspended license; or if they fail to retain information related to the provided service for two years.

## 35. <u>Registration and Identity Verification Service Providers License</u>

1/ Any Certificate Service Provider shall be obliged to provide Registration and Identity Verification Service, either by itself or through representative.

2/ Without prejudice Sub-Article (1) of this Article, any person who wants to engage only as a Registration and Identity Verification Service Provider may lodge application to the Root Certificate Authority.

**፴፮. <u>የምዝገባና ማንነት ማጣራት አገልግሎት ሰጪ ፍቃድ ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>**

ሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣኑ፡-

፩/ የምዝገባና ማንነት ማጣራት አገልግሎት ፍቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻን በተመለከተ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፤

፪/ ፍቃድ ያገኙ የምዝገባና ማንነት ማጣራት አገልግሎት ሰጪዎችን ዝርዝር በድረ- ገፁ ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል።

**፴፯. <u>የምዝገባና ማንነት ማጣራት አገልግሎት ፍቃድ አሰጣጥ</u>**

፩/ ሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣን የሚቀርብለትን የምዝገባና ማንነት ማጣራት አገልግሎት ፍቃድ ማመልከቻ የሚከተሉትን መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ እና በመመርመር፡-

ሀ) ለሚደርስ ጉዳት የሚውል የመድን ዋስትናን ጨምሮ የፋይናንስና ካፒታል አቅም፤

ለ) የሰው ሃይል ቁጥር እና የትምህርት ደረጃ፤

ሐ) የሃርድዌርና ሶፍትዌር ስርዓት ደረጃ፤

መ) አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልገው እውቅትና ተያያዥ ልምድ፤

ሠ) አገልግሎቱን ለመስጠት የሚከተለው ስነ-ስርዓት ደህንነት፤

ረ) የመስሪያ ቦታ ደህንነት፤

ሰ) የግል መረጃ ጥበቃና አጠቃላይ የመረጃ አያያዝ ደህንነት ፖሊሲዎች፤ እና

ሸ) የአደጋ ማገገሚያ እና የስራ ቀጣይነት ስትራቴጂ፤ ፈቃድ ይሰጣል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተመለከቱ መስፈርቶችን በተመለከተ ሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣን ዝርዝር መመሪያ ያወጣል።

**36. <u>Application for Registration and Identity Service Providers License</u>**

The Root Certificate Authority shall:

1/ Issues detail directive regarding registration and identity Service Provider license application;

2/ list licensed time-stamping service providers on its website.

**37. <u>Registration and Identity Service Provider Licensing</u>**

1/ The Root Certificate Authority shall examine and provide license for Registration and Identity Service License Application submitted based on the following requirements:

a) The required finance and capital capacity including insurance bond for future damage;

b) The required manpower and educational level;

c) The required hardware and software system;

d) The required knowledge and related experience to provide service;

e) The required system security to provide service;

f) The security of the service center;

g) Policies pertaining to custody of information security and personal data protection; and

h) Disaster recovery and work continuity strategy.

2/ The Root Certificate Authority shall issue detail Directive regarding requirements identified on Sub-Article (1) of this Article.

## ፴፰. <u>የምዝገባና ማንነት ማጣራት ፍቃድ የማያሰጡ ሁኔታዎች</u>

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፯ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተደነገገው ቢኖርም፣ የምዝገባና ማንነት ማጣራት ፍቃድ እንዲሰጠው ማመልከቻ ያቀረበው አካል፡-

ሀ) የተፈጥሮ ሰው፣

ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ ያልተቋቋመ ተቋም፣ ወይም

ሐ) በወንጀል የተፈረደበት ሆኖ የወንጀል ቅጣቱን ከፈጸመ በኋላ ያልተሰየመ፣

እንደሆነ ዝርዝር ምርመራ ሳያስፈልግ ማመልከቻው ውድቅ ይሆናል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ፍቃድ የማያሰጡ ሌሎች ሁኔታዎችን በተመለከተ ሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣን መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

## ፴፱. <u>የምዝገባና ማንነት ማጣራት ፍቃድ ዘመንና ተያያዥ ጉዳዮች</u>

፩/ የምዝገባና ማንነት ማጣራት ፍቃድ ወይም እውቅና ያገኘ አገልግሎት ሰጪ ፍቃዱ ለአምስት (፭) አመታት የሚያገለግል ይሆናል።

፪/ የሪፖዚቶሪ ፍቃድ ስለሚታደስበት፣ ስለሚታገድበት፣ ስለሚሰረዝበት፣ስለሚመለስበት እንዲሁም የፍቃድ መሰረዝ ውጤትን አስመልክቶ እንደአግባብነቱ በአዋጁ አንቀፅ ፲፫ ጀምሮ እስከ ፲፯ ያሉ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

## ፵. <u>የምዝገባ እና ማንነት ማጣራት አገልግሎት ሰጪ ግዴታዎች</u>

፩/ ማንኛውም የምዝገባ እና ማንነት ማጣራት አገልግሎት ሰጪ፡-

ሀ) አገልግሎቱን በሚሰጥበት ጊዜ ደህንነቱ የተጠበቀና አስተማማኝ ሥርዓትና ምርቶች የመጠቀም ሃላፊነት፣

## 38. <u>Conditions for Denying License</u>

1/ Notwithstanding Article 37 Sub Article(1) of these Regulations, any application to registration and identity license shall be rejected, without going into detail screening, if the applicant:

a) Is a natural person;

b) Is a body corporate not established in Ethiopia; or

c) Has been convicted of an offence and not reinstated after the completion of the punishment.

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, the Root Certificate Authority may prescribe Directive for additional qualification requirements to deny a license.

## 39. <u>License Period and Related Matters</u>

1/ A Licensed or recognized registration and identity services provider license is valid for five (5) years.

2/ The provisions of Article 13 through 17 of the Proclamation regarding license renewal, suspension, cancellation and return, as well as the consequences of cancellation, shall as appropriate, apply to registration and identity license.

## 40. <u>Obligations of Registration and Identity Verification Service Provider</u>

1/ Any Registration and Identity Verification Service provider has obligations:

a) To use a secured and trustworthy system and product while providing the service;

ለ) በሶፍትዌር፣ ሃርድዌር ወይም ስልተ ቀመር ላይ ማንኛውም ለውጥ ወይም ማሻሻያ ከማድረጉ በፊት ሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣኑን ማስፈቀድ፤

ሐ) ሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣኑ ወይም ሩት ሰርተፊኬት ባለስልጣኑ ፍቃድ የሚሰጠው ኦዲተር ኦዲት ሲያደርግ የመተባበር፣ ግዴታ አለበት፤

፪/ ማንኛውም የምዝገባና ማንነት ማጣራት አገልግሎት ሰጪነት ፍቃድ ለማግኘት ማመልከቻ የሚያቀርብ አመልካች ትክክለኛና የተሟላ መረጃ የመስጠት ሀላፊነት አለበት።

## ፵፩. የምዝገባና ማንነት ማጣራት አገልግሎት ሰጪዎች ተጠያቂነትና ቅጣት

፩/ በሕግ ወይም በውል ስምምነት የተቀመጡ ሌሎች ሃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም የምዝገባና ማንነት ማጣራት አገልግሎት ሰጪ በአዋጁ እና በዚህ ደንብ እንዲሁም ደንቡን ተከትለው በሚወጡ መመሪያዎች ላይ የተቀመጡ ግዴታዎችን ባለመወጣቱ ምክንያት ለሚያደርሰው ጉዳት ሃላፊ ይሆናል።

፪/ ማንኛውም የምዝገባና ማንነት ማጣራት አገልግሎት ሰጪ የፀና ፍቃድ ሳይኖረው፣ ወይም በታገደ ፍቃድ የምዝገባና ማንነት ማጣራት ስራዎችን የሰራ እንደሆነ ወይም ከሚሰጠው አገልግሎት ጋር ተያይዞ መረጃዎችን ለሁለት ዓመት ይዞ ካልቆየ ከ ብር አንድ መቶ ሺህ እስከ ሁለት መቶ ሺህ ይቀጣል።

b) To request permission from the Root Certificate Authority before making any modification to the hardware, software system or algorithm;

c) To cooperate for audit to be conducted by the Root Certificate Authority or an Auditor authorized by the Root Certificate Authority;

2/ Any applicant applying for a registration and identity service provider license shall have the duty to provide accurate and complete information.

## 41. Liability and Penalty of Registration and Identity Service Providers

1/ Without prejudice to other liabilities provided by contract or law, any registration and identity Service Provider who fails to meet its obligation under the Proclamation, these Regulations, and Directive issued following the Regulation shall be liable for the damage.

2/ Any registration and identity service provider shall be penalized with a fine ranging from one hundred thousand Birr to two hundred thousand Birr if they operate registration and identity services without a valid license; or if they operate registration and identity services with a suspended license; or if they fail to retain information related to the provided service for two years.

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፵፪. መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ይህን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስችል መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

**፵፫. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች**

ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

**፵፬. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፭ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም.**

**አብይ አህመድ (ዶ/ር)**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## PART SIX

## Miscellaneous Provisions

**42. Power to issue Directive**

Information Network Security Administration may issue Directive necessary to implement this Regulation.

**43. Inapplicable laws**

Any Regulations, Directives or Customary Practices which are inconsistent with the provisions of this Regulation shall be inapplicable with regard to matters covered under this Regulation.

**44. Effective date**

This Regulation shall enter into force as of the date of publication.

**Done at Addis Ababa, on the December 24th day of 2025.**

**ABIY AHMED (Dr.)**
**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**